# ለፖለቲካ ተቺዎች እና አስተቺዎች ትንሽ ምክር

ከመዝገበ ባየህ

እኔም እገሌም ሁሉም ተነስቶ በአቢይ ጉዳዮች ላይ የፖለቲካ ትችት ሊሰጥ ይችላል ማለት ስህተት ነው።

በቅድሚያ ስለጉዳዩ በቂ ግንዛቤ መያዝ ያስፈልጋል። የቱኒዚያው ህዝባዊ አመጽ ከፈነዳ ጀምሮ ራሳቸውን የፖለቲካ ተንታኝና ተቺ ያሉ ግለሰቦች (በአብዛኛው ዶክተሮች) በየመድረኩ የሚሰጡት ትንተና ስለ ተባለው ሀገርም ሆነ ሁኔታው ያላቸው ዕውቀት ከሰሞኑ ዜና ሁተታ ውጪ አለመሆኑን አርጋግጧል። ይህ ደግሞ አንባቢና አዳማጭ ካላችው አደናጋሪ ያደርጋቸዋል። ፈረንጆች ትንሽ ዕውቀት አደገኛ ነው ይላሉ። አላዋቂ ሳሚ እንደሚባለው ሳያውቁና ሳይመራመሩ መጽሐፍ ቅዱስ አጠባ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። የሀገራችን ፖለቲካ መድረክ በአውቅን ባዮች ጩኸት የተደናቆረ በመሆኑ፤ ስለድርጅትም ሆነ ማደራጀት ግንዛቤ ያጠራቸው አሰባሳቢና አስተማሪ ነን ብለው ተደርድረዋል። ለፖለቲካ ቱሪስቶች፣ ለፖለቲካ ኪስ አውላቂዎች፣ ለፖለቲካ ቁጭ በሉዎች ወዘተ የተመቻቸን ይመስላል። ይኸ ድክመታችን መታረሙ የግድ የሚለው ደግሞ የምዕራቡ ዓለም የልዕለ-ሃያልነቱን በትረ-ሥልጣን ያለተፎካካሪ በያዘበትና ያለይሉኝታ የግል ብሄራዊ ጥቅሙን በሚያሳድድበት ዘመን ላይ መገኘታችንና ወያኔን የመሰለ ፀረ-ኢትረዮጵያ ማፍያ ቡድን የሚገዛን መሆኑ ነው።

ባሰኛቸው ተቺዎች የሆኑትን ሁሉ የሚቀድም አለ እንበላቸው። ጎብዝ፡ እቴ ቶሽ፡ ረጋ በሉ መባል የሚገባቸው፣ ትላንት ከሕዝብ ጠላት ጎን ቆመው ታጋዩን ሁሉ ሲያብጠለጥሉ ነበርና ቢያንስ አጥፍተን ነበር ቢሉ ደግ ይሆናል ለማለት ነው። ዶክተር እገሌ ነኝ ብሎ በኢትዮሚዲያ ድረ ገጽ ላይ በእንግሊዝኛ (ጥቂት አረብኛም ደብለቅ እያረገ!!) ትችት ማቅረብ የጀመረው ግለሰብ በአዲስ አበባ ሳለ ኔሽን ይባል በነበረ የወያኔ ጋዜጣ ኢሕአዴግ ከወደቀ ኢትዮጵያ ትፈራርሳለች ብሎ በመናገር ሕዝብን ያስቀየመ ሆኖ ሳለ፣ ወያኔ የሚለውን "ክቡር ስም የኢሕአፓ ማፍያ አረከሰው" ብሎ ንደትና ቁጭቱንም በሌላ የወያኔ መጽሔት ገልጾ የነበር ሳለ፣ አንድም ጊዜ ግን ተሳስቼ ነበርን ሳያሰማ ቀስ በቀስ መለስን ዛሬ ከተሰደደበት ቦታ ሆኖ በማውገዝ ብቻ የሕዝብን ጎራ ሊቀላቀል ተነስቷል። ሕዝብን ይቅርታ ያልጠየቁ የቀይ ሽብርና ነጻ እርምጃ ወንጀለኞችም ሀፍረትን ቀብረው የፈረደበትን ኢሕአፓ ማውገዝ ብቻ ሳይሆን በአብይ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ተቺ ነንና አዳምጡን ሊሉን ተነስተዋል። እነዚህን ዓይነት ተቺዎች ዝም አይነቅዝም መባል አለባቸው እንጂ የወያኔ አጃቢዎች ሕዝብን መካሪና አስተማሪ ተደርገው ሊወሰዱ አይገባቸውም። ከወደ ካምፓላ፣ ዩጋንዳ ክፍሉ ሁሴን ብለው የሚጽፉት አዛውንቱ አቶ ክፍሉ ታደሰ ከሆኑም ምክራቸው ለቅንጅትም አልበጀና ከትችት በፊት ያለፈን ስህተት ሁሉ መመርመርና ከዚህም ተምሮ አደብ መግዛቱ ይሻላል ሊባሉ ይገባል።

ከትችት በፊት ዕውቀት አስፈላጊ ነው። በፖለቲካ እሳት ካየው ምን ለየው አይሰራም። በፖለቲካ ዝርዝር ኪስ አይቀድም። ተጨባጩን ሁኔታ ከሁሉም አቅጣጫ መመርመርና ማገናዘብ ተገቢ ነው። ቱኒዝያና ኢትዮጵያ ሁኔታቸው ያው ነው ማለት ሳይሆን ልዩነታችውን በተለይ አውቆና በአጽንኦት መርምሮ ተገቢውን ትምህርት መቅሰም ይገባል።

የሀገራችንን የአሁን ሁኔታ ከሰሜን አፍሪካው የሰሞኑ ህዝባዊ እምቢታ አንፃር ስንመረምርም፣ ትላንት ያለፍንበትን የእራሳችንን ታሪክ ልብ ማለቱ ጥሩ ነው። ከሰሜን አፍሪካዊያኑ ወንድም እህቶቻችን ብቻ ሳይሆን ከራሳችንም ብዙ ለዛሬ የሚጠቅሙን የትግል ተመክሮዎቹ አሉና። የቱን የቱን የህብረተሰባችንን ክፍል በምን በምን መንገድና እንዴት በማሳተፍ፣ መሬት አንቀጥቅጥ እምቢታ ማስነሳት ይቻላል? ብለን በመጠየቅ ሕዝባችን እስከዛሬ በመስዋዕትነት የፃፈውን ታሪክ ብንመረምር መልስ እናጣም። ተማሪዎች፣ አስተማሪዎች፣ እናቶች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ዕድሮች፣ ሰራተኞች ወዘተ ባለፍንባቸው የትግል ዓመታት የአደረጉት ተሳትፎና ጥቅም ላይ የዋሉት የትግል ስልቶች አሁን ካለንበት ሁኔታ ጋር ተገናዝበው ሥራ ላይ ሊውሉ ይችላሉ።

ይህን ስናደርግ ግን ነገረ-ሥራችን "ተኩላ የበጓ መጽሐፍ ገላጭ ሆነ" እንዲሉ እንዳይሆን ልንጠነቀቅ ይገባል። የወያኔና ጌቶቹ እንዲሁም ፀረ-ኢትዮጵያ መስመር አፍቃሪ ከሆኑ ተቺዎች ወይም የህዝብ መገናኛ ዘዴዎች ዕናት ያለው ህዝባዊ አቋምን መጠበቅ የለብንም። ወይንም ጠብቀን እራሳችንን ማታለል የለብንም። ወያኔ ወያኔን ብቻ ሆኖ አይደለም የሚታገለን፣ በአስመሳይነት እኛንም እየመሰለ እንጂ። ትግሉ እየገፋ ሲመጣ፣ የጠላትም መወራጨት ያንኑ ያህል ይበረታል እና በህዝብ ግንኙቱ መስመር አሰላለፋችንን አስተካክለን ማጠናከር አለብን። ነገ የሰሜን አፍሪካው አይነት የህዝብ እምቢታ ቢፈነዳ እውነታውን በበሰለ አእምሮ የሚያቀርቡ በቂ ተንታኞችም ሆኑ ቃል አቀባዮች አሉን ወይ? የተለያዩ ማህበረሰባዊ የህዝብ መገናኛዎችን (ሶሻል ሚዲያ) ጨምሮ ምን ያህል የተጠናከረና የሰፋ የመገናኛ አውታር አለን? ከሌሎች የመገናኛ አውታሮች ጋርስ ምን ያህል ትስስር/ግንኙነት አለን? ዴሞክራሲያዊው የአንድነት ጎራው በራሱ ውስጥስ ምን ያህል የተቀናጀና የተጠናከረ፣ አጀንዳ የመቅርፅና ትልም/የመሄጃ መስመር የማስያዝ አቅም አለው? ወዘተ የሚሉትን ጥያቄዎች እያነሳን መልስ መስጠት አለብን። በተደናበሩ ወይም ለማደናበር በአቀዱ ተቺዎችና የሙተቻ መድረኮች የተጣበበው የተቃዋሚው ጎራ ይህን ጉዳይ ቆም ብሎ ማሰቢያው አሁን ይመስለኛል።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!